# ስምህን ውሰድ*

በዋልክበት ላልውል፥ ላልጉዋዝ ባለፍክበት
ራእይህን ላልጋራ፥ በውጥንህ ላልጸናበት
ለሀገሬ ላልሠራበት
ወገኔን ላልጠቅምበት
አንተን ላልሆን ላልመጥንህ
ተራርቄ ከመንፈስህ
ስምህን ብቻ ተሸክሜ
ያላቅሜ . . .
ከመሥዋዕትነትህ ላልቁዋደስ
በሰማ¦ትነትህ ላልታደስ
ወኔህ ወደኔ ላይጋባ
ዕንባህ ፈንቅሎኝ ላላነባ
ከFመምህ ተካፍዬ
በቁጭትህ ተቃጥዬ
ከጥላህ ስር ተጠልዬ
ከጀግንነት ማዕድህ ላልሳተፍ ጠጋ ብዬ
አለሁ . . . ስምህን ብቻ ተሸክሜ
ያላቅሜ።
ላልሆን አንተ እንደሆንከው
ዋጋ ላልከፍል ከከፈልከው
ላልጥር እንደታገልከው
በጽናት እንደኖርከው
በጽናት እንዳለፍከው
ግርማ ሞገስህ ላይኖረኝ የጉብዝና ስጦታህ
የቆራጥነት ገጽታህ
ተሸከምኩት ስምህን
ላልመስልህ አንተን ላልሆን።
የተደመርኩበት ትውልድ የተፈጠርኩበት ዘመን
አንተን አጥቶ አንተን ናፍቆ እያሰበህ በሰመመን
የሞትክላትን ገድሎዋት
ያስከበርካትን አስንቁዋት
ያዋሃድካትን ገንጥሎዋት
የቆምክላትን ረግጦዋት
እኔም አለሁ . . . በስያሜህ ተከትቤ
አንድ አድራጊነትክን ተርቤ
ስምህን ብቻ አንግቤ
አለሁ . . . ባዶ እጄን ቆሜ
ስምህን ብቻ ተሸክሜ
ያላቅሜ።

___________________
ለግርማዊ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ 130ኛ ዓመት ኅልፈተ-ህይወት መታሰቢያ የተጻፈ
ከቴዎድሮስ አበበ
ሚያዝያ 1990 ዓ.ም.፥ April 1998

---

* ይህ ግጥም ፈተና በሚል ር¦ስ በቅርቡ ካሳተምኩት መጽAፍ (http://www.tewodros.com) ገጽ 139-140 ላይ የተወሰደ ነው። እነሆ የአጼ ቴዎድሮስን 138ኛ ዓመተ እረፍት በዚህ በያዝነው የሚያዝያ ወር እናስበዋለን። ከዚሁ ጋር አብረን የሕዝብ ድምፅ እንዲከበር በቆራጥነት ታግለው የተሰዉትንና በወያኔ ወህኒ ቤቶች በግፍ የሚማቅቁትን፤ ለፍትሕ፥ ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የቆሙትን ጀግኖች በአክብሮት እናስባቸዋለን። የሀገራችንን አንድነትና የሕዝብዋን ነፃነት የሚያከብርና የሚያስከብር ኢትዮጵያዊ መንግሥት ለማየት ያበቃን ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳን።

ቴ.አ.
ሚያዝያ 1998 ዓ.ም.፥ April 2006